የትምህርት ታዳሚያንን ወደ ትምህርት ገበታ ለመመለስ የተዘጋጀ

የተግባቦትና አድቮኬሲ ትግበራ መመሪያ

በትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ

2013 ዓ.ም

ባህር ዳር

ዳራ

ትምህርት ቢሮ በ2013 ዓ.ም ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የተሰሩ ስራዎችን መልካም ተሞክሮዎች በማስፋት
እና ድክመቶችን በመለየት በቀጣይ የትምህርት ዘመን ነባር እና በተለያዩ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ እንዲሁም እድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ ወደ ትምህርት ቤት ያለመጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ የተለያዩ የኮሚኒኬሽን ስራዎችን ለመስራት አቅዷል።

አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ትግበራ መመሪያ አጠቃላይ አላማ ትምህርት ቢሮ እና በየደረጃው በትምህርት ዘርፉ ላይ ያሉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ የየበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ነው።

ዝርዝርዓላማዎች

- የትምህርት ቢሮ ባለድርሻ አካላት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ አስፈላጊውን ሀብት ለማሰባሰብ ተገቢውን ሚና የሚጫወቱበት መመሪያ በመስጠት የትግበራ ሰነድ ሆኖ ማገልገል።
- ማንኛውም ባለድርሻ አካል መመሪያውን መሰረት ያደረገ የተግባቦት እና የአድቮኬሲ መሳሪያዎችን በመጠቀም ደረጃውን የጠበቀ ስልታዊ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት የመመለስ ንቅናቄ እንዲያካሂዱ ማስቻል።
- በትምህርት ዘርፉ ላይ ያሉ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ማቀናጀት እና ማስተባበር።

ግንባር ቀደም ተተኳሪ አካላት(ሴቶችን ጨምሮ)

- እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ እና ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ተማሪዎች
- ከትምህርት ገበታቸው በተለያዩ ምክንያት ያቋረጡ ተማሪዎች
- ተፈናቃዮች (በተለያዩ ምክኒያቶች በሀገር ውስጥ እና በክልሉ የተፈናቀሉ፣ ስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች)
- በከተማ ያሉ አቅመ ደካማ ቤተሰብ ልጆች እና የተጎዱ አካበባቢዎች
- በገጠር በግብርና ስራ የተሰማሩ የቤተሰባቸውን ኑሮ የሚደጉሙ ህፃናት እና ወጣቶች
- በአካል ጉዳት እና የተለያዩ ማህበራዊ ጫናዎች ሰበብ የተገለሉ ህፃናት።

የታዳሚዎች ክፍፍል

ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ በሚደረገው የኮሚኒኬሽን እና የማሳመን ስራ የሚከተሉት ታዳሚዎች ግንባር ቀደም ናቸው ።

- ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወላጆች እና አሳዳጊዎች
- የትምህርት ቤት አስተዳደር፣መምህራን እና የወላጆች፣ የመምህራን እና የተማሪዎች ጥምር ኮሚቴ
- የማህበረሰብ ክፍሎች(ሴቶች እና ወጣቶችን አካቶ)
- መምህራን ማህበርና ሌሎች አደረጃጀቶች
- የሀይማኖት ድርጅቶች፣ ማህበረሰባዊ መሪዎች እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች
- የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አመራሮች
- የሲቪክ ማህበራት (የአካል ጉዳተኛ ማህበራትን ጨምሮ)

- በተለያዩ ምክንያቶች በሀገር ወስጥ የተፈናቀሉ፣ ስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች የማህበረሰብ አካላት እና ህፃናት።

ቁልፍ መልእክቶች በታዳሚዎች ክፍፍል

ተማዎችን ወደ ትምህርት ገበታ ለማምጣት/ለመመለስ በሚደረገው የተግባቦት እና የዘመቻ ስራዎች የሚከተሉት ቁልፍ መልእክቶች በተለያዩ ይዘቶች ተዘጋጅተው ለተተኳሪ ታዳሚያን በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች ተደራሽ የሚደረጉ ይሆናሉ።

ከተተኳሪያን ታዳሚያን አንፃር የተቀመጡ ቁልፍ መልዕክቶች

ቁልፍ መልእክት	ተተኳሪ ታዳሚያን	የትግበራ ስልት እና ምርመራ
• በትምህርት ቤቶች ሊተገበሩ ስለሚገቡ የኮቪድ ፕሮቶኮሎች	• የትምህርት ቤት አስተዳደር ፣መምህራን እና የወላጆች፣ የመምህራን እና የተማሪዎች ጥምር ኮሚቴ • ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወላጆች እና አሳዳጊዎች	• በሀገር አቀፍ ደረጃ በጤና ሚኒስቴር እና ህብረተሰብ ጤና ኢኒስቲቲዩት የተቀመጠውን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ተጠቀም • መልዕክቶችን እንደየ ታዳሚያኑ አይነት ማዘጋጀት
• ማንኛውም ወላጆች ወይም አሳዳጊ ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ ይላኩ ወይም ይመልሱ።	• ወላጆች ፣ማህበረሰቡ እና አጋሮቹ (የ ሀይማኖት/ የእምነት ድርጅቶች የመሳሰሉት)	• የማህበረሰብ አጋሮች ልየታ ማድረግ • መልዕክቶችን እንደየ ታዳሚያኑ አይነት ማዘጋጀት

• ማንኛውም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ ለማምጣት/ ለመመለስ ሁኔታቸውን በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጪ አመቻች ያድርጉ።		
• እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ እንዳይመጡ/ እንዳይመለሱ የሚያደርጉ መሰናክሎችን ያስወግዱ (የህፃናት ጋብቻ፣ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ፣ የፆታ ጥቃት ወ.ዘ.ተ)	• ወላጆች፣ ማህበረሰቡ ፣ የትምህርት ቤት የፆታ ክበባት አባላት እና ሌሎችም፣ እንዲሁም የእድር አባላት።	• በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ አካላትን መጋበዝ • ጉዳዮችን በመቅረፅ በተለያዩ አውታሮች ለሰፊው ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ።
• ለተገለሉ ቡድኖች ህፃናት የትምህርት መሰናክል የሆኑ ጉዳዮችን የመወያያ አጀንዳ አድርጉ። • የትምህርት ቤትን አካባቢ ምቹ እና ፆታዊ ምላሽ የሚሰጡ ያድርጉ	• የትምህርት አስተዳደር/ አመራሩ ፣ የትምህርት ቤት የፆታ ክበባት፣ የመንግስት አካላት፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ፣ የወላጆች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ማህበራት፣ የህግ አስፈፃሚ አካላት እና የሲቪክ ማህበራት፣	• የወላጆች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ማህበራት ስበሰባዎች • በየደረጃ የሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ስብሰባዎች ቅድመ ዝግጅት ማድረግ

	በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የሴቶች፣ ወጣቶች እና ህፃናት ዘርፍ።	
• ዛሬ የተማረ ልጅ ለነገው ቤተሰብ ዋልታ ነው	• ወላጆች/ አሳዳጊዎች ፣ ማህበረሰቡ	• በትምህርት ቤት ሰዎች ሊመለከቱ በሚችሉበት አካባቢዎች በፖስተር፣ ባነር በመሳሰሉት መልዕክቶቹን ማኖር እና በትምህርት ቤት መክፈቻ ቀን በትምህርት ቤቶች አካባቢ ማስተዋወቅ።
• ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ/ እንዲመለሱ የየድርሻችንን ሃላፊነት እንወጣ	• ማንኛውም የህብረተሰብ አካል	• በየደረጃው ለሚካሄዱ የትምህርት ጉባኤዎች፣ ሰብሰባዎች፣ ስልጠናዎች እና በመሳሰሉት መድረኮች አጀንዳ አድርጎ መተግበር።
• ሁሉንም የመማሪያ እና የማስተማሪያ አማራጮች ይጠቀሙ (የርቀት ትምህርት፣ ኦንላይን ትምህርት፣ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የትምህርት፣ የገፅ ለ ገፅ ትምህርት)	በትምህርት ስርኣት ውስጥ የሚገኙ የዘጎ ት/.ት መምሪያዎች ፣ የወረዳ ት/ት ፅ/ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች የትምህርት ማዕከላት።	• ሰብሰባዎች ፣ ስልጠናዎች ፣ ኮንፍረንሶች ወ.ዘ.ተ መጠቀም
•		

ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ለትምህርተ የደረሱ ህፃናትን በመለየት ከሚመለከታቸው ጋር በማገናኘት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ/ እንዲመለሱ አድርጉ።	መምህራን፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር የማህበራዊ እና ማህበረሰብ ሰራተኞች፣ የወላጆች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ጥምርታ፣ ሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች ጉዳዮች መምሪያዎች እና ፅ/ቤቶች.	ከአከባቢያዊ ማህበራዊ ሰራተኛ እና ከ ሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶ መምሪያና ጽ/ቤት ጋር በመወያየት በቅንጅት መስራት።
አካባቢያዊ ሁበት በማሰባሰብ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ እና አስፈላጊ መሰረተ ልማት እንዲሟሉ ያድርጉ።	የትምህርት ሴክተሩ፣ በየደረጃው ያሉ የመንግስት የዞን፣ የወረዳ፣ መምሪያዎች እና ፅ/ቤቶች፣ባለሀብት፣ ማህበረሰቡ	በየደረጃው ካሉ የዘርፉ አካላት እና አጋሮች ጋር ውይይት ማድረግ እና የድርጊት መርሃ ግብር ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ።
በትምህርት ዘርፉ ላይ ያሉ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የክትትል እና የሪፖርት ስርዓት ይዘርጉ።	በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ዘርፉ አጋሮች	በየደረጃው ባሉ ቋሚ ዘናዊ፣ ወረዳዊ የግንኙነት መድረኮችን መጠቀም በየወቅቱ(አመታዊ፣ መንፈቃዊ፣ የሩብ አመት፣ ወራዊ መድረኮች) ማከናወን

የተግባቦት ሰንጠረዥ

እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ ለማምጣት/ ለመመለስ በሚደረገው እንቅስቃሴ በተለያየ ይዘት ለተለያዩ ተተኳሪ ታዳሚያን የሚዘጋጁ መልእክቶችን በሚከተለው የተግባቦት አግባብ እና ማሰራጫ ተደራሽ የሚደረግ ይሆናል።

የተግባቦት መሳሪያዎች	ተተኳሪ ታዳሚያን	ማሰራጫ	የትግበራ ስልት እና ምርመራ
ፕረስ ኮንፍረንስ (ሃላፊዎች፣ ቃል አቀባዮች)	ጠቅላላው ማህበረሰብ	• ኤሌክትሮክስ ሚዲያ(ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ) • ማህበራዊ ሚዲያ(ፌስቡክ፣ ቴሌግራም) • የህትመት ሚዲያ (ጋዜጣ)	• በክልል/ዞን ደረጃ የሚተገበር
ሁነቶች (ወደ ትምህርት ገበታ መመለስ፣ አዳዲስ ስራዎች ማስጀመሪያ፣ የትምህርት ምዝገባ ቀናት፣ አመታዊ ቀናቶች(የመምህራን	ጠቅላላው ማህበረሰብ	• ኤሌክትሮክስ ሚዲያ(ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ) • ማህበራዊ ሚዲያ(ፌስቡክ፣ ቴሌግራም) • የህትመት ሚዲያ (ጋዜጣ)	• በክልል እና በየደረጃዉ በሚገኙ የትምህርት መዋቅሮች የሚተገበር • ሰዎች በሚሰበሰቡበት ስፍራ ህዝባዊ ዘመቻ ማካሄድ

እውቅና ቀን፣ ዓለም አቀፍ የልጅ አገረጾች ቀን፣ አለም አቀፍ የሰቶች ቀን እና ሌሎች መሰል ተከባሪ ቀናት.			
የሚዲያ አጫጭር መልዕክቶች	ወላጆች እና አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ ማህበረሰብ፣ የትምህርት አመራር፣ ተማሪዎች፣ የሲቪክ ማህበራት	• ኤሌክትሮክስ ሚዲያ(ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ) • ማህበራዊ ሚዲያ(ፌስቡክ፣ ቴሌግራም)	• እንደየ አካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚዘጋጅ • መልዕክቶችን እንደየ ታዳሚያኑ አይነት ማዘጋጀት
ሰብሰባዎች	የፖለቲካ አመራሮች ፣ አጋር ድርጅቶች፣ የህፃማኖት አባቶች እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቡ	• ገፅ ለ ገፅ • የቀጥታ (ኦንላይን)	• በተለያዩ ደረጃዎች የሚዘጋጁ ስበሰባዎች
ዜናዎች፣ ፕሮግራሞች ፣የፓናል ውይይቶች እና የቀጥታ የስልክ ልውውጥ ፕሮጋራሞች	ጠቅላላው ማህበረሰብ	• ሚዲያ(ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ) • ማህበራዊ ሚዲያ(ፌስቡክ፣ ቴሌግራም)	• በወቅቱ የሚዲያ ተቋማቶች የሚዲያ ሽፋን እንዲሰጡ እና መረጃዎችን እንዲያሰራጩ መጋበዝ
ዘመቻ	ተማሪዎች፣ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ	• ቤት ለቤት ጉብኝት • ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ (ቴሌቪዥን ና ራዲዩ)	• በክልል፣ በዞን በወረዳ እና በትምህርት ቤት ደረጃ የሚተገበር

		• ማህበራዊ ሚዲያ (ፌስቡክ፣ ቴሌግራም) • የትምህርት ቤት የተለያዩ መርሃግብሮች(ሰልፎች፣ ውድድሮች፣ ፌስቲቫሎች ወ.ዘ.ተ)	
የማህበረሰብ ውይይት	ማህበረሰቡ፣ወላጆች ፣ የተለያዩ ማህበራት(የመምህራን፣የሴቶች፣ የወጣቶች ማህበራት፣ታዋቂ ባህላዊ መሪዎችእና ተዕዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች)	የወላጆች፣ የ መምህራን እና የተማሪዎች ጥምርታ ኮሚቴዎች፣እድር፣ እቁብ፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የአካባቢ ስብሰባዎች	• እንደየ አካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚዘጋጅ • መልዕክቶችን እንደየ ታዳሚያኑ አይነት ማዘጋጀት እና ተደራሽ ማድረግ
የህትመት ውጤቶች	ወላጆች እና አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ	ፖስተር ፣ ባነር ፣ ቢልቦርድ	• መልዕክቶችን እንደየ ታዳሚያኑ አይነት ማዘጋጀት እና ተደራሽ ማድረግ

ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ ለማምጣት እና ለመመለስ የምንከተላቸው የተግባቦት ደረጃዎች

1 ወደ ትምህርት ገበታ የሚመጡ /የሚመለሱ ህፃናት አይነት ቡድኖችን (ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች፣ አቅመ ደካማ ቤተሰብ ልጆች እና የተጎዱ አካበባቢዎች፣ አካል ጉዳተኞች ወ.ዘ.ተ)መለየት

2 ችግሩን ነቅሶ ማውጣት- በቡድኑ አይነት(ለምሳሌ፥- ለትምህርት የደረሱ የተፈናቃይ ቤተሰብ ህፃናት) ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ገበታ ያልመጡበትን /ያልተመለሱበትን ምክኒያት እንደየ ቡድኑ ሁኔታ መለየት

3 እንደየ ቡድኑ ተደራሽ የሆነ የመገናኛ አውታር መምረጥ (ምሳሌ- መስማት ለተሳናቸው የምልክት ቋንቋ፣ ለ ተፈናቃዮች ባሉበት ተደራሽ የሆነ የመገናኛ ዘዴ(ድምፅ ማጉያ) ወ.ዘ.ተ

4 እንደየ ተደራሽ ቡድኑ አይነት መልእክቶችን መንደፍ

- ✓ የቅድመ ሙከራ መልዕክቶችን ማዘጋጀት
- ✓ ቅድመ ሙከራ ማካሄድ
- ✓ ዋና መልዕክቶችን ማዘጋጀት እና የማህበረሰብ ውይይት አጀንዳ መንደፍ (በተወያዮች የሚመነጭ)
- ✓ መልዕክቶችን ማሰራጨት/ ተደራሽ ማድረግ (በተለያዩ መገናኛ አውታሮች)
- ✓ በመጨረሻም ክትትል እና ግምገማ ማካሄድ በኢትዮጵያ ያሉ የመገናኛ ዘዴዎች

ተ.ቁ	የመገናኛ ዘዴዎች አይነት	ሀገር አቀፍ	ክልል	ማህበረሰብ እና ትምህርት ቤቶች
1.	ቴሌቪዥን	ኢቲቪ፣ ፋና፣ ዋልታ፣ ኢቢኤስ ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ቴሌቪዥን	የአማራ ቴሌቪዥን ጣቢያ	

2.	ራዲዮ	ሀገር አቀፍ እና ኤፍኤም ራዲዮኖች	• የክልል ራዲዮኖች እና ኤፍ ኤም ራዲዮኖች • የክልል የትምህርት ራዲዮ ጣቢያዎች	የማህበረሰብ ራዲዮ
3.	ማህበራዊ ሚዲያ	የትምህርት ሚኒስቴር ድህረ ገፅ፣ ፌስቡክ እና ቴሌግራም ገፆች	የክልል የትምህርት ቢሮ ማህበራዊ ሚዲያዎች እና የሌሎች የመንግስት ድህረገፆች፣ ፌስቡክ፣ እና ቴሌግራም ገፆች	የትምህርት ቤት የቴሌግራም ገፅ እና ፌስቡክ
4.	ሚኒ ሚዲያ	----------	---------	የትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ
5.	የማህበረሰብ ፎረም	----------	----------	እድር፣ እቁብ፣ ማህበር እና ሌሎችም
6.	የሀይማኖት ፣ የእምነት እና የባህላዊ ግንኙነት መድረኮች	ሀገር አቀፍ የሀይማኖቶች ጉባኤ	ክልል አቀፍ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ	የሀይማኖት የትምህርት ፕሮግራሞች(ሰበካ መድረክ፣ የሰንበት ትምህርት፣ የጁኡማ እና ኩትባ ሌሎችም)

ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ ዘመቻ ዋና ባለድርሻ አካላት

ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ ለማምጣት እና ለመመለስ በሚደረገው ዘመቻ ዋና ተዋናይ የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር ተግባር እና ሃላፊነት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ተ.ቁ	ባለድርሻ **አካላት**	ተግባር እና ሃላፊነት	ከክልል ት/ት ቢሮ፣ከዞን እና ከከተማ አስተዳደር ት/ መምሪያዎች፣ ከወረዳ ት/ጽ/ቤቶች የሚጠበቁ	የክንውን የጊዜ ሰሌዳ
1.	የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ	• ክልል አቀፍ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሱ የተግባቦት እና የ አድቮኬሲ መመሪያ እና ስታንዳርድ ማዘጋጀት እና ማሰራጨት	----------	መስከረም ወር መጀመሪያ
		• ዘመቻውን የሚያስፈፅሙ አብይ እና ቴክኒካል ኮሚቴዎችን ማቋቋም እና ስራውን ማስጀመር		ከነሀሴ መጨረሻ በፊት
		• ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ ዘመቻን ማስተባበር ፣		

		ለዞን እና ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች በደረጃው የ ሚያስፈልጋቸውን ሃብት እና ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት		
		• ለሚዲያ ተቋማት ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ ዘመቻ ላይ ግንዛቤ መፍጠር እና ከሚዲያ ቷማት ሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት ማስተዋወቅ		
		• ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ዘመቻ ማከናወን እና የዘመቻውን የጊዜ ሰሌዳ ማውጣት ማዘጋጀት		
		• ክልል አቀፍ ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ ዘመቻን በሁነት ቀናት ውስጥ አካቶ እንዲተገበር ማስተባበር እና		

		ሁነቶችን በክል አቀፍ ደረጃ ማዘጋጀት		
		ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ ለማምጣት እና ለመመለስ የሚረዱ የተለያዩ አጫጭር የሚዲያ መልዕክቶች፣ ዜናዎች፣ ፕሮግራሞች እና የ ፓናል ውይይቶችን ማዘጋጀት እና ተደራሽ ማድረግ።		
		• ለዞን እና ለ ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች ስለ ዘመቻው ስትራቴጂ፣ መመሪያ እና ፕሮግራሞች ኦረንቴሽን መስጠት		
2.	የሚዲያ ተቋማት(የክልል እና የ ትምህርት ሚዲያዎች)	ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ ዘመቻን የሚዲያ ሽፋን መስጠት	ስለ ዘመቻው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት፣ መጋበዝ እና ማከናወን። ስሜት አነሳሽ ድርጊቶች ያሉበትን ቦታ መለየት እና መጠቀም	ከ ዘመቻው መጀመሪያ አንስቶ
		ስሜት አነሳሽ ደርጊቶችን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች መቅረፅ እና ተደራሽ ማድረግ	ሚዲያ ግብዕት የሚሆኑ መረጃዎችን መስጠት እና ሁነቶችን መጠቀም	

		ዘመቻው ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ፓናል ውይይቶች እና ለሌሎች ፎርማቶች የአየር ጊዜ ማመቻቸት።.		
3.	የጤና ቢሮ እና መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች	• የኮቪድ 19 ፕሮቶኮሎችን የመከለስ እና ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ • የኮቪድ-19 ግንዛቤን ለማሳደግ በትምህርት ቤቶች የጤና ባለሙያዎችን መመደብ •	• መደበኛ ትምህርት የሚጀመርበትን የጊዜ ሰሌዳ • የኮቪድ-19 ለመከላከል የሚያስችሉ አቅርቦት ማድረግ • በትምህርት ቤቶች የኮቪድ 19 መከላከያ ያልተሟላላቸው ትምህርት ቤቶች መረጃ	የመደበኛ የትምህርት ጊዜ ከመጀመሩ በፊት
4.	የውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ቢሮ እና መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች	• በትምህርት ቤቶች የውሃ አቅርቦት ማሟላት • ለትምህርት ቤቶች የውሃ አገልግሎት መስጫ ፋሲሊቲ መጠገን ፣ ለሌላቸው የማቋቋም አገልግሎት መስጠት።	• የውሃ አቅርቦት የሌለባቸው ትምህርት ቤቶች መረጃ • በትምህርት ቤቶች የኮቪድ 19 መከላከያ ያልተሟላላቸው ትምህርት ቤቶች መረጃ ማዘጋጀት እና ለሚመለከተው መስጠት	

5.	የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች ቢሮ/መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች	• ከትምህርት ቢሮ እና ከትምህርት መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች ጋር በዘመቻው መሳተፍ • ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ(ልጃገረዶችን ጨምሮ) ማሰስ፣ መመዝገብ እና ማስተባበር ስራዎች ላይ መሳተፍ። • ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ከትምህርት ገበታ ወጪ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን መከታተል ፣ መለየት እና ከሚመለከተው አካል ጋር መስራት።	ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ህፃናት ቁጥር መረጃ በዖታ እና በመልካ ምድራዊ አድራሻ ማስቀመጥ	አመቱን ሙሉ
6.	የልማት አጋሮች እና ሲቪክ ማህበራት	• ለዘመቻው ቴክኒካዊ እና የገንዘብ ድጋፍ መስጠት • ለህብረሰተቡ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት	• ትምህርት ቤቶች የሚከፈቱበትን የጊዜ ሰሌዳ • የዘመቻው ስትራቴኪ ዶክመንት እና ከትምህርት ቢሮ የሚጠበቁ መረጃዎች • ሌሎች አስፈላጊ ፣ መመሪያዎች ወ.ዘ.ተ ከቢሮዉ መዉሰድ	አመቱን ሙሉ

7.	የዞን እና ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች	• ክልል አቀፍ ህፃናትን ወደትምህርት ቤት ለማምጣት እና የመመለስ ዘመቻው ሰነድ ወደ ራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ማዘጋጀት • በዞን እና ከተማ አስተዳደሩ ዘመቻውን የሚያስፈፅሙ አብይ እና ቴክኒካል ኮሚቴዎችን ማቋቋም እና ስራውን ማስጀመር • ለዘመቻው በዞን እና ከተማ አስተዳደሩ ያሉ ትምህርት ቤቶች፣ እና ወረዳዎችን ማስተባበር ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት ። • በዞን እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የዘመቻ ሁነቶችን ማዘጋጀት፣ ማስተባበር እና የድርጊት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት	የትምህርት ታዳሚያንን ወደ ትምህርት ገበታ ለመመለስ የተዘጋጀውን የተግባቦትና አድቮኬሲ ትግበራ መመሪያ ማውረድ። ለዘመቻው በዞን እና ከተማ አስተዳደሩ የሚያስፈልጉ የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፎችን መስጠት ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ወደ ትምህርት ገበታ የማምጣት እና የመመለስ ዘመቻ ሁነቶች የጊዜ ሰሌዳ ለዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች ማሳወቅ እና መላክ።	አመቱን በሙሉ መስከረም ወር አመቱን በሙሉ ከመስከረም መጀመሪያ ሳምንት ጀምሮ አመቱን በሙሉ

		• በክልሉ ቋንቋ የዘመቻውን አጫጭር መልዕክቶች፣ ፕሮግራሞች፣ ዜናዎች፣ ውይይቶች ማካሄድ እና ማሰራጨት	ቁልፍ የዘመቻው መልእክቶችን እና የሚዲያ አጀንዳዎችን ወደ ዞን እና ከተማ አስተዳደሩ ማሳወቅ እና መላክ	

የመገናኛ ዘዴዎች ክትትል ግምገማ እና ስነዳ

- በክልል አቀፍ ሚዲያዎች የሚተላለፉ የሚዲያ ሽፋን በይዘት እና በአድማስ መከታተል (በትምህርት ቢሮ የኮሚኒኬሽን የስራ ዘረፍ ባለሙያዎች ፣ በዞን እና በከተማ አስተዳደር ያሉ የኮሚኒኬሽን የስራ ዘረፍ ፎካሎች የሚከወን ይሆናል።)
- የተሳሳቱ እና የተዛቡ መረጃዎችን በወቅቱ የእርምት እርምጃዎች ማድረግ
- የተለያዩ የሚዲያ መልእክቶች ከመሰራጨታቸው በፊት መገምገም እና እንደ አስፈላጊነቱ እርማት ማድረግ እና ማሰራጨት(የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እና የክፍሉ ባለሙያዎች እና በየደረጃው ያሉ ማህበራዊ እና ባህሪ ለውጥ ግብረ ሃይል)
- በሚዲያ የተላለፉ ዜናዎችን፣ አጫጭር መልዕክቶችን እና ትምህርታዊ ስሜት አነሳሽ ዘገባዎችን መሰነድ (የትምህርት ቢሮ የኮሚኒኬሽን የስራ ዘረፍ ባለሙያዎች ፣ በዞን እና በከተማ አስተዳደር ያሉ የኮሚኒኬሽን የስራ ዘረፍ ፎካሎች የሚከወን ይሆናል።)